# የዘረኛነት ወረርሽ

ሰሞኑን አንድ የንግድ ተቋማት ማስተዋወቂያ ቡክሌት ደርሶኝ ተገርሜ እያየሁት ነው፡፡ መጽሔቱ ክርስቲያን ነጋዴዎችን የያዘ መሆኑን ገና ከመግቢያው ይገልጣል፡፡ ክርስቲ ያኖች እርስ በርሳቸው ሊረዳዱ እንደሚገባ፣ የጌታ ልጆች በአንድነት መኖር እንዳለባቸው፣ ከዚያም አልፎ አንዱ ከሌላው በመግዛት ወይንም በመጠቀም ወንድማማችነትን እንዲያሰፍኑ፣ ያም ለምድሪቱ በረከት መሆኑን በጥቅስ እያዋዛ ይገልጣል፡፡

እየገረመኝም እየደነነገጥኩም ነበር ያነበብኩት፡፡ በኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ዘረኛነት ይህንን ያህል ሥር ሰድዷል ማለት ነው? አልኩ ለራሴ፡፡ ለመሆኑ ይህቺ ሀገር በስንት ዓይነት ዘረኛነት እንድትሰቃይ ይሆን የተፈረደባት? ስልም ጠየቅኩ፡፡ ዛሬ በዚያች ሀገር «ገንዘባችን በየክልላችን» ብቻ ሳይሆን በየቋንቋችንም በመግባት ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የሚለው እየቀረ የኦሮምያ፣ የአማራ፣ የደቡብ፣ የትግራይ፣ የሶማልያ ባንኮች ብቅ ብቅ እያሉ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ ደግሞ በይፋ ስማቸውን ባይገልጡም በአንድ እምነት ሥር ያሉ ሰዎችን ብቻ በአክስዮን የሚያሰባስቡ ባንኮችም እየታዩ ነው፡፡

ዘረኛነት ማለት እንዴው በቀላሉ ሲገለጥ አንድን ሰው በዕውቀቱ፣ በችሎታው፣ በዐቅሙ፣ በትምህርት ደረጃው ወይንም በሌላ መለኪያ ሳይሆን በወገንተኛነቱ ብቻ መመዘን ማለት ነው፡፡ ወይንም ደግሞ ወገንተኛነትን ከሌሎች መለኪያዎች ሁሉ አልቆ መመልከት ማለትም ይሆናል፡፡

*ሀገርሽ ወዴት ነው ብዬ ብጠይቃት*

*ከም ከም ብላ ሳቀች ነገሩ ቢደንቃት፣ አይደለ ብሂሉ*

ዘረኛነት ለአንዲት ሀገር በሽታዋ ሲሆን ነገሮችን ሁሉ በግለሰባዊነት ወይንም ደግሞ በጋራ ጥቅሞች እና አስተሳሰቦች ሳይሆን በአንዳች የቡድን መልክ ብቻ ማየት ይጀመራል፡፡ ዘረኛነት በመወለድ እና በክልል፣ በጎሳ እና በሀገር ልጅነት ብቻ የሚከሰት አይደለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ መልከ ብዙ ገጽታ ነው ያለው፡፡ የጎሳ፣ የፓርቲ፣ የሃይማኖት፣ የማኅበር፣ የሠፈር፣ ወዘተ ዓይነት ዘረኛነቶች አሉ፡፡

የጎሳውን ዓይነት ዘረኛነት በውጭም በውስጥም ያለን የዚህች ሀገር ሰዎች ጠግበነዋል፡፡ የት ተማርክ? ከሚለው ይልቅ የት ተወለድክ? የሚለው ጥያቄ አሰልችቶናል፡፡ ምን ትችላለህ ሳይሆን ምን ትናገራለህ? ሆኗል መመዘኛችን፡፡ አንድ ሰው የእገሌ ጎሳ አባል በመሆኑ ምክንያት ይወደዳል፣ ይጠላል፡፡ ይከበራል፣ ይናቃል፡፡ ሥራ ያገኛል፣ ሥራ ያጣል፡፡ ይኮራል፣ አንገት ይደፋል፡፡ ዕድል ይከፈትለታል፣ ዕድል ይዘጋበታል፡፡ ይሾማል፣ ይሻራል፡፡

*ሳቅና ጨዋታ ዝና ካማራችሁ*

*እንደኛ እንትን ላይ በተወለዳችሁ*

የሚለው ዘፈናችንኮ ጤነኛ እንዳይመስላችሁ:: ሳቅ፣ ጨዋታ እና ዝናን ለማግኘት አትችሉም እያለን ነው:: ለምን ብንለው ከኛ ሀገር አልተወለዳችሁማ፤ ምን አማራጭ አለን:: መልሰን አንወለድ::

ሌላ ቋንቋ ሲሰሙ ጆሯቸውን የሚያሳክካቸው፤ ፊታቸው የሚለዋወጥ፣ ንዴት ንዴት የሚላቸው እንዳሉ ሁሉ፤ ያንን ቋንቋ ሲሰሙ ቸርነታቸው ሁሉ የሚከፈት፣ መስተንግዷቸው የሚሟሟቅ፣ አድሏዊነታቸው የሚጨምርም አሉ::

የጎሳ ዘረኛነት ሥር ከመስደዱ የተነሣ ሕዝቦችን ለማቀራረብ እና ለማግባባት ከምንሠራው ሥራ ይልቅ ልዩነታቸው እንዲገባቸው የምንሠራው ሥራ ይበልጣል:: እንደ ኢትዮጵያን በመሰለች ብዙ ቋንቋዎች በሚነገርባት ሀገር አንድ ተማሪ ከሥራ ቋንቋ ውጭ የራሱን አካባቢ ቋንቋ ብቻ ነው የሚማረው:: ከዚያ ውጭ የሚማረው እንግሊዝኛ ነው:: ከአካባቢው ቋንቋ ውጭ ያለውን የሚያስተምሩት መምህራንም አንዳንድ ጊዜ የጠላት ሀገር ቋንቋ የሚያስተምሩ ይመስል ወይ እነርሱ በግዴለሽነት ያስተምራሉ አለያም አካባቢያቸው በንቀት ያያቸዋል::

በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሕዝብ የሚናገራቸው ቋንቋዎች አሉ:: አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ ሶማልኛን የመሰሉ:: አንድ ተማሪ ከአካባቢው ቋንቋ በተጨማሪ ቢቻል ሌሎች ሁለት ካልተቻለም አንድ የሌላ አካባቢ ቋንቋ መርጦ እንዲማር ቢደረግ እንዴት መልካም ነበር:: በመጀመርያ ደረጃ ጥላቻውን ያስቀረዋል:: ሰው የሚያውቀውን ነገር የመጥላት ሁኔታው ዝቅተኛ ነውና:: በሁለተኛ ደረጃም ያግባባናል:: አንዳንዴኮ ከተወለድንበት እና ካደግንበት ክልል ውጭ መሄድ ውጭ ሀገር እንደመሄድ እየሆነብን ነው?

አንድ የሶማሌ ሰው (6.0% ተናጋሪ አለው) አማርኛ (32.7% ተናጋሪ አለው) እና ኦሮምኛ (31.6% ተናጋሪ አለው) ቢችል ከስድሳ በመቶ በላይ ከሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ይግባባል ማለት ነው:: ይህም አንዱ ወደ ሌላው ሄዶ የመሥራት፣ ተጋብቶ እና ተዋልዶ የመኖር ብሎም ከሌላው ወገኑ ጋር ልብ ለልብ የመግባባት ዕድሉን ይጨምረዋል:: እንግሊዝኛ በትምህርት ቤቶቻችን ያለውን ክብር ግማሽ ያህል የሀገራችን ሌሎች ቋንቋዎች የላቸውም::

ይህንን አመለካከት ቀርፈው ሕዝቡን ልዩነት ወደሚከበርበት አንድነት ያመጡታል የሚባሉት የፖለቲካ ልሂቃንም ራሳቸው ዘውገኞች ሆነዋል:: አብዛኞቹ ፓርቲዎቻችን ጎሳን ወይንም አካባቢን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ያንን ፓርቲ በአሠራሩ፣ በአመለካከቱ እና በፖለቲካ ፕሮግራሙ ብትወዱት እንኳን እንደገና እዚያ ክልል ገብታችሁ ለመወለድ ባለመቻላችሁ ብቻ ከአባልነት ትታቀባላችሁ::

www.danielkibret.com

የሀገሬ ሰው «መወለድ ቋንቋ ነው» የሚለው እዚህ ላይ አይሠራም፡፡ መወለድ እኛ ሀገር ቋንቋ ብቻ አይደለም፡፡ ፓርቲም፣ ሥራም፣ ሹመትም፣ ገንዘብም፣ መሬትም፣ ርእዮተ ዓለምም ጭምር ነው፡፡ እስካሁን ድረስ አንድን ወገን ነጻ የሚያወጡ አያሌ ድርጅቶች አሉን በሀገራችን፡፡ ማን ማንን ከማን ይሆን ነጻ የሚያወጣው? አማራው ከትግሬው፣ ትግሬው ከአማራው፣ ኦሮሞው ከአማራው፣ አማራው ከኦሮሞው ነው ነጻ የሚወጣው? እየተጨቋቆንን ነው የምንኖረው ማለት ነው?

አንዳንዶቹ ፓርቲዎች እኛ ሕዝቡን ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ነው ነጻ የምናወጣው ይላሉ፡፡ መቼም ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ነጻ መውጣትን የሚጠላ የለም፡፡ ግን ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ነጻ ለመውጣት የግድ ነጻ አውጭ ፓርቲ ያስፈልገናል? በዓለም ላይ ራሳቸውን ከድህነት አረንቋ ያወጡ ሕዝቦች አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ በነጻ አውጭ ፓርቲዎች ነው እንዴ ነጻ የወጡት?

ፓርቲዎቻችን የጎሳ ዘረኝነትን ብቻ አይደለም የፓርቲ ዘረኝነትንም መላቀቅ አልቻሉም፡፡ ከራሴ ፓርቲ አባል ውጭ ያለው ሁሉ ስሑት፣ ፀረ ልማት፣ ጨቋኝ፣ አንድነትን የሚያናጋ፣ አገር አጥፊ፣ ጠላት፣ ከሀዲ፣ ለሀገር የማይጠቅም ነው ብሎ ማሰብ ነው የፓርቲ ዘረኝነት፡፡ ሰውን በፓርቲ አባልነቱ ብቻ ማድነቅ፣ መውደድ፣ መሾም እና ማግነን ነው የፓርቲ ዘረኝነት፡፡ ሰውን በፓርቲ አባልነቱ መጥላት፣ ማነወር፣ ማራቅ እና ማግለል ነው የፓርቲ ዘረኝነት፡፡

በርግጥ በአሁኑ ጊዜ በሕዝባችን ዘንድ ሰውን ብቻውን ማየት ከባድ እየሆነ መጥቷል፡፡ ሰው በቡድን ውስጥ ነው የሚታሰበው፡፡ በፓርቲው፣ በጎሳው፣ በእምነቱ፣ በክልሉ፣ በሚኖርበት አካባቢ፣ በሥራ ዓይነቱ፣ ነው የሚታየው፡፡ እገሌ ሳይሆን እነ እገሌ የሚለው ድምፅ ነው የሚሰማው፡፡

ከምድራዊ ነገር ይልቅ ሰማያዊውን የሚሰብኩት፣ ፍቅር እና ሰላም ዋና አጀንዳዎቻቸው የሆኑት የእምነት ተቋማት እንኳን ሳይቀሩ በዘረኝነት አረንቋ ውስጥ ሰምጠውበታል፡፡ በአንድ በኩል የእምነት ዘረኝነት በሌላ በኩል ደግሞ የጎሳ ዘረኝነት እያላጋቸው ነው፡፡

አንድ ሰው በንግዱ፣ በአገልግሎቱ እና በሞያው መመረጥ ያለበት ባለው ችሎታ፣ ዕቅም እና ጥራት መሆን ነበረበት፡፡ አሁን አሁን ግን የኛው እምነት ሰው መሆኑ የበለጠ ቦታ እየተሰጠው መጥቷል፡፡ ሙስሊሙ ሙስሊሙን ነጋዴ፣ ክርስቲያኑም ክርስቲያኑን ነጋዴ እንዲመርጡ የሚቀሰቅሱ ጽሑፎች እየወጡ ነው፡፡ ከዚያም አልፈው የንግድ እና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በሃይማኖታቸው ዘውግ ብቻ ከፍለው ከእነዚህ ብትገዛ ይመረጣል እያሉን ነው፡፡ ገንዘባችን በየእምነታችን እንዲሆን እየተሰበከን ነው፡፡

ትምህርት ቤቱ ጥራቱ እንዴት ነው? የሚለው ቀርቶ ሙስሊም ነው የከፈተው ወይስ ክርስቲያን? ኦርቶዶክስ ነው የከፈተው ወይስ ፕሮቴስታንት ሆኗል ጥያቄው፡፡ መርፌውን በየእምነታችን ሊወጉን

የተዘጋጁ የሕክምና ተቋማትም ብቅ ብቅ እያሉ ነው፡፡ በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች ለመቀጠር የአንድ እምነት ተከታይ መሆን ብቻ ከትምህርትም፣ ከልምድም በላይ ዋጋ ሲኖረው እያየን ከመገረም አልፈን ለምደነዋል፡፡

የእምነት ተቋማቱ ከዚህም አልፈው የጎሳውን ዘረኛነት የሚያባብሱ ተቋማትም ሆነዋል፡፡ ጎጃሜ ጎጃሜውን፣ ጎንደሬ ጎንደሬውን፣ ትግሬ፣ ትግሬውን፤ ኦሮሞ ኦሮሞውን፣ ወሎ ወሎዬውን ሲስበው ማየት ለተቋማቱ ቅርብ ለሆነው ብቻ ሳይሆን ርቆ ላለው ምእመናቸውም የዕለት ዜና ሆኖለታል፡፡ የአንደኛው ወገን በእምነት ተቋማቱ የሥልጣን እርከን በወጣ ቁጥር፣ የእምነቱን ተከታዮች ከማብዛት ይልቅ የወንዙን ልጆች ማብዛት ዋናው ተልዕኮው እየሆነ ነው፡፡

መካ ላይ አላሁ አኩብር ያለው ቢላል ኢትዮጵያዊ እንጂ ሳዑዲያዊ አለመሆኑ ተረስቷል፡፡ ደብረ ዳሞ ላይ የሚከብሩት አቡነ አረጋዊ የአውሮፓ ሰው እንጂ ኢትዮጵያዊ እንዳልነበሩ ተዘንግተዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ሰውን በሰውነቱ ብቻ ተቀብለው የሚያስተናግዱበት፣ በእምነቱ ከመሰላቸው ሀገራቸውን ሀገሩ አድርገው የሚሰጡበት ዘመን እንዳይቀር ያሰጋል፡፡

ስንቶች ከሌላ ክልል ብቻ ሳይሆን ከሌላ ሀገር መጥተው፣ ትውልዳቸውንም ረስተው ኢትዮጵያውያን ሆነው ቀርተዋል፡፡ «እኔስ በሀገሬ እንኳን ሰው ወፍ አለምዳለሁ» ነበር የምንለው፡፡ ዛሬ ይሄ ተረት ሊሆን ነው መሰለኝ፡፡ አቡነ አረጋዊን ትግሬ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስንም አማራ አድርጎ የሚያይ ትውልድ እየመጣ ነው፡፡ ሁለቱም ግን እንኳን እና ትግሬ እና አማራ ኢትዮጵያዊም አይደሉ፡፡

ልጁ ሊቀጠር ወደ አዲስ አበባ ይመጣል፡፡ ታድያ መካሪዎች «ስትሄድ ጳጳሱ የሀገራቸውን ሰው ይቀጥራሉና ሀገርህ የት ነው ካሉህ ያንተን አትናገር የርሳቸውን ሀገር ተናገር» ብለው ይነግሩታል፡፡ ታድያ ጳጳሱ ፊት ሲቀርብ የሀገራቸው ስም ጠፋው አሉ፡፡

እንደገባ

«ሀገርህ የት ነው?» አሉት

«የርስዎ ሀገር» አላቸው፡፡

«የኔ ሀገር የት ነው?» አሉት

«ከኔ ሀገር» አላቸው አሉ፡፡ ምን ያድርገው፡፡

www.danielkibret.com

አንዳንዶችማ ከዚህም ወርደው ወርደው የቆብ ዘረኛነትም ውስጥ ገብተዋል፡፡ ሕጋውያን ካህናት ከታላላቅ አድባራት አስተዳዳሪነት እንዲወገዱ ዐዋጅ ያወጣው ማን ይሆን? ዛሬ ለሹመት ዋና መመዘኛው መመንኮስ ሆነና «መነኮሰ ሞተ» የሚለው ትርጓሜ «መነኮሰ በላ» ወደሚለው ዞረ፡፡ በዚህ የቆብ ዘረኛነት ምክንያትም መመንኮስ የሌለባቸው ለሥራ እና ለሹመት ሲሉ እንዲመነኩሱ አንዳንዶችም ሚስቶቻቸውን ደብቀው እንዲመነኩሱ አደረግናቸው፡፡ በተለይም የውጩ ሀገር ዕድል ሁሉ ከሕጋውያን ይልቅ ለመነኮሳቱ እጅግ ክፍት እየሆነ ሲመጣ፣ ያልገባቸው እና ያልተገባቸው መነኮሳት እየበዙ መጡ፡፡

ከዚህም አልፎ ምንኩስናዊ ሕይወቱ ሳይሆን የት መነኮሰ? የሚለው የዘረኛነት መለኪያ እየሆነ ነው፡፡ እናም የት ብመነኩስ የምንኩስናን ተጋድሎ እፈጽማለሁ? መባሉ ቀርቶ የት ብመነኩስ ቶሎ ሹመት አገኛለሁ? ሆነ ጥያቄው፡፡

«የኛ ልጆች» የሚሉ የማኅበርተኞችን የዘረኛነት ቋንቋስ ሰምታችሁ አታውቁም፡፡ ዛሬ ዛሬ አያሌ ማኅበራት እየተፈጠሩ ነው፡፡ የሃይማኖት፣ የጉዞ፣ የሞያ፣ የበጎ አድራጎት፣ የከብካቤ፣ የሌሎችም ማኅበራት፡፡ አንድን ሥራ ለማከናወን አንድነት መፍጠሩ መልካም ሆኖ ሳለ ዘረኛነቱ ግን ከፋ፡፡ «እንዲህ ሲል ያውካል» አለ ተርጓሚ፡፡ የሰውን ስሕተተኛነት እና ትክክለኛነት ከማኅበራቸው አባልነት አንፃር ብቻ የሚተነትኑ ማኅበርተኞች አሉ፡፡

***ይህን የመሰለ ቁመና ይዘሽ***

***ምናለ ፈጣሪ የኛ ባረገሽ***

የሚለው ሀገርኛ ዘፈን ትርጉሙ የገባኝ አሁን ነው፡፡

ምን መልካም ብትሠሩ፣ ምን ተአምር ብትፈጽሙ እነርሱ ከገቡበት ካልገባችሁ ሥራችሁ ሁሉ የመርገም ጨርቅ ይሆናል፡፡ ምን ተሠራ? ሳይሆን ማን ሠራው? ነው ለእነርሱ ቁም ነገሩ፡፡ በማኅበር ይወዳሉ፣ በማኅበር ይጠላሉ፣ በማኅበር ያቀርባሉ፣ በማኅበር ያገላሉ፣ በማኅበር ያጸድቃሉ፣ በማኅበር ይኮንናሉ፣ በማኅበር ይረዳሉ፣ በማኅበር ይነፍጋሉ፡፡ አባል ከሆናችሁ ሁለት እና ሁለት አምስት ይሆንላችኋል፤ አባል ካልሆናችሁ ግን እንኳን አምስት አራት አይሆንላችሁም፡፡

በጎ ነገር ስትሠሩ ካዩዋችሁ ሊያበረታቷችሁ እና ሊያግዟችሁ አይደለም የሚፈልጉት፤ ሊያደንቋችሁ እና ሊያመሰግኗችሁ አይደለም የሚተጉት፤ አባል ሊያደርጓችሁ እንጂ፡፡ ምክንያቱም ከማኅበራቸው ውጭ በጎ ነገር ሲሠራ ማየት ስለማይፈልጉ፡፡

ዘረኛነት የሁላችንም ጠባይ እየሆነ ነው፡፡ ከጎሳው ብናመልጥ፣ ከፓርቲው፣ ከፓርቲው ብናመልጥ ከእምነቱ፣ ከእምነቱ ብናመልጥ ከማኅበሩ ጎጠኛነት ውስጥ መገኘታችን አልቀረም፡፡ ይህ ሁሉ ሰዎች በሥራቸው፣ በሞያቸው፣ በልምዳቸው፣ በችሎታቸው፣ በዐቅማቸው፣ በጥንካሬያቸው፣ በትጋታቸው እና በጥረታቸው ሳይሆን በአንዳች ወገንተኛነታቸው እንዲመዘኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ወልጋዳ ሚዛን ደግሞ ወዳጆችን እንጂ ጎበዞችን፣ ወገንተኞችን እንጂ ሊቆችን ዕድል አይሰጥም፡፡

አገር የምታድገው በብርቱ ባለ ሞያዎች፣ በተመራማሪ ወጣቶች፣ በለውጥ አምጭ ምሁራን፣ በችግር ፈቺ የፈጠራ ሰዎች፣ በሥጋት ሰባሪ ነጋድያን፣ በሃሳብ አመንጭ ሊቆች እንጂ በተሰባሰቡ ወገንተኞች አይደለም፡፡ ያማ ቢሆን በየወገናችን ለሺ ዓመታት ያህል ተሰባስበን አልነበር?

***አሌክሳንድርያ፣ ቨርጂንያ***

www.danielkibret.com